አንዳችሁ ወንድሙ ላይ መሳሪያን አይደቅን። አይታወቅም ምናልባት ሸይጧን መሳሪያውን ከእጁ ላይ ይወሰውሰውና በእሳት ጉድጓድ ውስጥ ሊጥለው ይችላልና።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው
ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል፦ "አንዳችሁ ወንድሙ ላይ መሳሪያን አይደቅን። አይታወቅም ምናልባት ሸይጧን መሳሪያውን ከእጁ ላይ ይወሰውሰውና በእሳት ጉድጓድ ውስጥ ሊጥለው ይችላልና።" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) አንድ ሙስሊም ወደ ሙስሊም ወንድሙ ማንኛውንም የመሳሪያ አይነት ከመደቀን አስጠነቀቁ። ምናልባት ሳይታወቀው እጁ ላይ ባለው መሳሪያው ሸይጧን ወስውሶት ወንድሙን እንዲገድል ወይም እንዲጓዳ ሊያደርገው ይችላልና። በዚህም የእሳት ጉድጓድ ውስጥ ወደ ለመጣል የሚያደርሰው ወንጀል ላይ ይወድቃል።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/66246